# ይድረስ ለለንደን አንበሶች

የመሄጃ ያለህ ዱካ ተከትሎ የሚያጠፋ መጣ
ከላያችን ሆኖ ዘለላው ሳይበስል የሚያረግፍ በቁጣ
መኖር ስላልቻለ ጧት ማታ እያመጡ ጣጣና ፈንጣጣ
ወገናችን ሁሉ ሳይመለስ ቀረ ካገሩ እንደወጣ

እኔን ውሃ ይብላኝ ውቅያኖስ ዋጣቸው አወይ ያምላክ ቁጣ
ያላባቷ ውርደት ያለናቱ ስደት በረሃ በላቸው ሚቀመስ ሲታጣ
የተኮለኮለው ያ ሃሞተ-ቢስ እርባና መች አለው እኛን ካላስቀጣ
ከዕድሜ ቀጥል ካድሬ ካአቫዩ-ጠንቋዩ አንሻም ገለጣ
ሕዝብም አዛባ አለው እድሜ ቀጥል ካድሬ
አሸርጋጁ ምሁር አባዩ ጥንቋዩ የሃገር ቅራሬ
ብን ቢሉ ባንድ ላይ እፎይታ ነበረ ላገሬ ለክብሬ

ሰይጣንነትማ ስለፈቀደው ነው ግዳጅ ሳይኖርበት
ይብላኝ ለሽፍጠኞች ችግር ለማይፈቱ እየሠሩ ስህተት
እዩት የኛን ወገን ልቡ ተቋጥሮ ፈጣሪ እርቆበት
መቸ ይሆን ከቶ:- ደስ የሚሰኘው ሕመሙ ቀርቶለት

እጅግ የታወቀው የአግአዚ አዛዥ ብርሃንን የሚያሸሽ
ይመስክር ጎዳናው ወጣቶችን ገዳይ ወላድ ጥቁር አልባሽ
ገደብ አበጅቶ ከፍ ያለውን ራዕይ እንዳንይዝ የሚጥር
ሥራው ሲገመገም ፀሃይ እንዳታበራ ይመስላል ሚሻጥር
እንኳን ፀሃይ ቀርታ የሌሊቷን ንግሥት ጨረቃን ሞክሯል
የሰማይ ከዋክብት እንዳያንፀብርቁ ሁሌ ያሰላስላል

በድፍን ሃገሩ ጨለማን የሚያነግስ ጥላ የሚያጠላ
ችግር ሳታባዛ ምነው ውሃ በሆንክ ገና ሳለህ ጫቅላ

ተፈጥሮ ሃብታሟ  ጥበብ ለግሳቸው ግን ያልተከረከሙ
በቀናኢ መንፈስ ሠፋ ደልደል እንዳልን-- እያዩ እየሰሙ
እየቆረጡ ጣሉት በማሺነሪያቸው ሃገር ሊያዳክሙ

ያንን አጥፊ ሜሽን ቀጥቅጡና አቅልጡት ባዲስ እንዲተካ
ሰንጥቁት ቁረጡት ሥሩበት ማረሻ ማጭድ ወይም ማንካ
አትጠራጠሩ ሲለውጥ ብቻ ነው ሕዝባችን ሚረካ

እየኖረው አይደል:-- ታላቅ መሆን ጠልቶ ትንሽነት ወዶ
ምክራችንን ንቆ ወደ አመዱ ትቢያው አሽቆልቁሎ ወርዶ
ሁላችን ዘብ እንቁም እንዳንቀለበስ ውዥንብር ሥር ሰዶ

በውስጥም በውጭም የደከማችሁት እናንት የኛ ሰዎች
ያስመሰከራችሁ ሃገር ወዳዶቹ የጋራ ዕቅድ አውጮች

ጎዳና ጠራጊ በታኝ አስወግደው መገንባት የሚያውቁ
ትግሉ ሳይቋረጥ በመቀጠላቸው ሁሌ ሚደነቁ
መስዋዕት ሊሆኑ ገና ከጠዋቱ ቆርጠው የተነሱ

በመስመር ቆመዋል በተሎ ሊደርሱ ሃገር ሳያፈርሱ

በነሎቹ ሃገር ድምፃቸው ተሰማ እጅግ በጣም ልቆ
በምድረ አውሮፓ ጀግና ተላልኮ መጣ ባጭር ታጥቆ
የሳጥናኤል መሪ በእብሪት ተወጥሮ አውሮፓ ሲመጣ
ምሱን አቀመሱት ኋጥያቱን ዘክዝከው እንዳይቀናጣ

ታሪካችን ይፃፍ የተሠራው ገድል ባውሮፓ ከተሞች
ድምፃችን ይመዝገብ ቁጣችንም ይታይ የኢትዮጵያውያኖች
ነሎቹ ያውቁታል ማን አፈራረሞ ነው ለወረደው ችግር
ለይቶ መግጠም ነው መንፈሳችን ፀንቶ ሳንቆም ወደ ዳር